የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/782

ቀን ኅዳር 20 ቀን 2015 ዓ.ም.

ለባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ

አዲስ አበባ፣

ጉዳዩ፡- **የቦርዱን ውሣኔ ስለማሳወቅ፤**

ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ነሐሴ 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ባ/ለ/ዲ00552 በተፃፈ ደብዳቤ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት ነሐሴ 15 ቀን 2015 ዓ.ም. መደበኛ ስብሰባውን በማካሄድ ያልተሟሉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ማሟላቱን እንዲሁም ነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ባ/ለ/ዲ/00566 በተፃፈ ደብዳቤ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2015 ዓ.ም. ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ መወሰኑን ለቦርዱ አሳውቋል።

ፓርቲው ያቀረበውን ሰነድ ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 እና ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንፃር በመመርመር ያልተሟሉ ጉዳዮችን አሟልቶ እንዲያቀርብ በ18/01/2015 በቁጥር አ1162/11/737 በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፆለት በ24/01/2015 ዓ.ም በቁጥር ባ/ለ/ዲ/00583 በተፃፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል።

ቦርዱ ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ የቀረበውን ሰነድ መርምሯል።

## I. የፓርቲውን ምክትል ሊቀመንበር ማፅደቅ በሚመለከት

የፓርቲው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በፕሬዚዳንቱ ተመርጠው ለብሔራዊ ምክር ቤት ቀርበው እንደሚጸድቁ፤ ከአባላት ውስጥ ፕሬዚዳንቱ ብቁ ናቸው ያላቸውን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ዝርዝርና የስራ ድርሻ ለብሔራዊ ምክር ቤት አቅርበው እንደሚያፀድቁ፤ ምክትል ፕሬዚዳንቱ በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት እንደሚመረጥ እና ተጠሪነቱም ለፕሬዝዳንቱ እንደሆነ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 16.1፤ 20.10 እና 20.2 ተደንግጓል።

በዚህ ረገድ የፓርቲው የቀድሞ ፕሬዚዳንት ፓርቲው ውስጥ በነበሩበት ጊዜም ይሁን ከፓርቲው አባልነትና አመራርነት መልቀቃቸውን በመግለጽ የፓርቲው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፤ በየደረጃው ያሉ የፓርቲው አመራር አባላት እና ሌሎች ከምክትል ፕሬዝደንቱ አቶ አምሀ ዳኜው ጋር ሙሉ በሙሉ በመተባበር ስራቸው



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ +251 115 153468
ፋክስ +251 115 510025
ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ www.nebe.org.et

የተቃና እንዲሆን እንዲተባበሯቸው ሐምሌ 16 ቀን 2014 ዓ.ም. ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደብዳቤ የፃፉ መሆኑን፤ ብሔራዊ ምክር ቤቱም ለሶስተኛ ጊዜ በ15/12/2014 ዓ.ም. ስብሰባ ተጠርቶ 12 አባላት በተገኙበት ስብሰባ አቶ አምሀ ዳኜው በሙሉ ድምፅ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲሰሩ መምረጡ ቦርዱ ተገንዝቧል።

## II. <u>የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ አጠራርን በተመለከተ</u>

በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 14.1 የፓርቲ ብሔራዊ ምክር ቤት እስከ 45 ቋሚ እና 15 ተለዋጭ አባላት እንደሚኖሩት፤ በአንቀፅ 14.2 ንዑስ አንቀፅ 2 ብሔራዊ ምክር ቤቱ የጠቅላላ ጉባኤውን መደበኛ፣ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች እንደሚጠራ፣ በአንቀፅ 19.7 ንዑስ አንቀፅ 1 በማንኛውም የፓርቲው ስብሰባ ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ እንደተሟላ እንደሚቆጠር፤ በንዑስ አንቀፅ 2 ደግሞ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ካልተሟላ ሶስተኛው ተጠርቶ በተገኙት አባላት እንደሚካሄድ ተደንግጓል።

ከዚህ አንጻር የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት ስብሰባን ለመጥራት ሚያዝያ 2 እና 6 ቀን 2014 ዓ.ም ተሞክሮ ምልዓተ ጉባኤው ስላልተሟላ ስብሰባው አለመከናወኑን የሚገልጹ ሰነዶች መቅረቡን፤ ብሔራዊ ምክር ቤቱ ለሦስተኛ ጊዜ በ15/12/2014 ዓ.ም. ተሰብስቦ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ መስከረም 29 ቀን 2015 ዓ.ም. እንዲደረግ በሙሉ ድምጽ መወሰኑን፤ በተጨማሪ ከ208 መስራች የጉባኤ አባላት ውስጥ ከ1/3ኛ በላይ አባላት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ የወሰኑበት ሰነድ ተሟልቶ መቅረቡን ቦርዱ ተመልክቷል። በመሆኑም የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤን ለመጥራት የሄደበት ሂደት የተሟላ በመሆኑ ቦርዱ ተቀብሎታል።

ስለሆነም ቦርዱ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት በ15/12/2014 ዓ.ም. ለሶስተኛ ጊዜ ተጠርቶ 12 አባላት በተገኙበት በሙሉ ድምፅ አቶ አምሀ ዳኜው ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሆኑ ያሰለፈው ውሣኔ በቦርዱ ተቀባይነት አግኝቷል። ስለዚህ የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር አቶ አምሃ ዳኜው ናቸው ሲል ወስኗል። እንዲሁም ፓርቲው በ29/01/2015 ዓ.ም. ለማድረግ ያቀደው ጠቅላላ ጉባኤ ቀኑ ያለፈ በመሆኑ በደንቡ መሠረት ተለዋጭ ቀን በመቁረጥ ለቦርዱ በማሳወቅ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያካሂድ ቦርዱ ወስኗል።

ከበጎ ምኞት ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
Deputy Chairperson National Electoral Board